22130011

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A: LITERATURE – STANDARD LEVEL – PAPER 1**
**AMHARIQUE A : LITTÉRATURE – NIVEAU MOYEN – ÉPREUVE 1**
**AMHÁRICO A: LITERATURA – NIVEL MEDIO – PRUEBA 1**

Wednesday 8 May 2013 (morning)
Mercredi 8 mai 2013 (matin)
Miércoles 8 de mayo de 2013 (mañana)

1 hour 30 minutes / 1 heure 30 minutes / 1 hora 30 minutos

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a guided literary analysis on one passage only. In your answer you must address both of the guiding questions provided.
- The maximum mark for this examination paper is *[20 marks]*.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Rédigez une analyse littéraire dirigée d’un seul des passages. Les deux questions d’orientation fournies doivent être traitées dans votre réponse.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est *[20 points]*.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un análisis literario guiado sobre un solo pasaje. Debe abordar las dos preguntas de orientación en su respuesta.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es *[20 puntos]*.





© International Baccalaureate Organization 2013

*ከሚከተሉት ምንባቦች **አንዱን** መርጠህ ስነጽሁፋዊ ትንታኔ ስጥ። ከታች የተቀመጡትን ጥያቄዎች መመለስ ይኖርብሀል።*

**1.**

ወሎ ከብት በብዛት የሚረባባት፣ እምቦሳ የሚቦርቅባት፣ አዝመራ እንደ ልብ የሚታፈስባት፣ አላፊ አግዳሚው እሸቱን ዝምግን የሚበላባት፣ አየሯ ለአዝመራ፣ ለእንሰሳትና ለነዋሪዎቿ ተስማሚ የሆነ ለም ሀገር ናት። ወሎ ሁለመናዋ ተወዳጅና ውብ ነው። ውሃው ተጠጥቶ አይጠገብም። ህዝቡ በመተሳሰብና በመከባበር ይኖራል። ወሎ በተለይ የፈረስና የቆነጃጅት ሀገር ናት እየተባለ ይነገራል። በእውነትም የወሎ ልምላሜና ውበት ለአይን ማራኪ ነው። አዝማሪው ስለ ወሎ ሲያዜም

በጥብጩ ልቀባው የወሎን አፈር
እኔም እንደነሱ ምናልባት ባምር
እንደምነው ወሎ አይጠገብዋ
ሁሉም ሰው አክባሪ ጥሪያቸው አይዋ ብሏታል።

ነገር ግን ምን ያደርጋል በወሎ ላይ የተመሰረተው የመሬት ስሪት ወሎንና የወሎን ህዝብ ለከፋ ርሃብና እልቂት ዳረገው። የወሎን የመሬት ስሪትና ያስከተለውንም የታሪክ ጠባሳ ቀደም ብዬ ገልጬ ዋለሁ። ወሎ ላይ በአንድ የተወሰነ ወቅት የመሬት ስሪቱን የተለያዩ ስሞች እየሰጡ ከዘር ወደ ዘር እርስት የተላለፈበትን የገበሬ መሬት እየነጠቁ ከሩቅ ለመጡ ትክለኞች መስጠት ተጀመረ። የመሬት ከበርቴዎችና መኳንንቱ የወሎን አርሶ አደር በዘበዙት፣ አራቆቱት፣ ፍትህ አልባም አደረጉት።

በተለይም ከጣሊያን ወረራ በኋላ ጠላት ካሠራቸው ውስጥ የደሴ ማተሚያ ቤት የሳሙናና የዘይት ፋብሪካ አለማጣ ላይ የነበረው የጥጥ ፋብሪካ ኮምቦልቻ አየር ማረፊያ የነበሩ የብረት ቤቶችና ሌሎችም የልማት ተቋሞች ወደሙ። ንብረታቸው እየተወሳለቀ ተሸጠ። ወሎ በጤና በትምህርትና በሌላውም መስክ ልማት ያልታቀደላት ክፍለ ሀገር ነበረች። ለዚህም ዋነኛው ምክንያቶች የሰገሌና የማይጨው ጦርነቶች ነበሩ። አጼ ምኒልክ ሲሞቱ የአልጋ ወራሻቸው ከልጃቸው ከሸዋረጋ ምኒልክና ከንጉስ ሚካኤል የሚወለዱት ልጅ እያሱ ነበሩ። ነገር ግን በወቅቱ ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ልጅ እያሱ ሰልመዋል ሀገሪቱን የእስላም ሀገር ሊያደርጋት ነው። ኢትዮጵያን ሊመሩ አይችሉም የሚል የሃሰት ፕሮፓጋንዳ በማስነዛት ከግብረ አበሮቻቸው ጋር ተመሳጥረው ስልጣናቸውን ገፈፉ። በዚህ የተበሳጩት አባታቸው ንጉስ ሚካኤል በድንገት የወሎ ጦራቸውን ይዘው ወደ ሸዋ ገሰገሱ። የአጼ ኃይለሥላሴ የጦር ሚኒስትር ፊታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ ጅማና ሀረር ያለውን ጦራቸውን እስከሚያሰባስቡ ድረስ ገብረናል፣ አምነናል፣ የሁለት ወንድማማቾች ደም መፍሰስ የለበትም እያሉ ንጉስ ሚካኤልን ሲያታልሉ ቆዩና ጥቅምት 9 ቀን 1990 ዓ.ም. ባልታሰበ ሰዓት አደጋ ጥለው ንጉስ ሚካኤልን ድል አደረጉ።

በማይጨው ጦርነት ደግሞ ንጉሱ ከማይጨው ሸሽተው በወሎ አድርገው ሲያልፉ በሰገሌ ጦርነትና የአገዛዙ አስከፊነት አስመርሮት የወሎ ህዝብ አደጋ ጣለባቸው። በበሽሎና በተንታ አድርገው ፊጦ ሲደርሱ የአካባቢው ህዝብ ጦርነት ገጠማቸው። ደጃዝማች ወዳጄ የአልጋ ወራሹ ሞግዚት ሆነው በዝብዘውት ስለነበር ደጃዝማች ወዳጄን አስረክቡን ስላሉ በመትረየስ ታጨደ።

አጼ ኃይለሥላሴ በወሎ ህዝብ ላይ ይህንን የመሰለ የቆየ ቂም ስለነበራቸው

«ወሎን በክፉም ሆነ በደጉ እናውቀዋለን።» እያሉ እስከ ስልጣናቸው ፍጻሜ ድረስ በወሎ ህዝብ ላይ ቂም ነበራቸው። ስለሆነም በወሎ ገበሬ ላይ ይደርስ የነበረው ግፍ እየበዛ ሄደ። አገዛዙ አስመረረው። ለም አፈሯ፣ ወንዞቿ፣ ተራሮቿና ያን መሳይ የተፈጥሮ ውበቷ ተራቆተ። ዋግ፣ ላስታ፣ ወረሂመኑ፣ ራያና ቆቦ፣ አላማጣና እንዲሁም ሌሎቹ ቆላማ አውራጃዎች በድርቅ ተመቱ። የወሎ ህዝብ አገሩን እየተወ መሰደድ ጀመረ።

*አመዴ ለማ ፣ ፊታውራሪ አመዴ ለማ፣* (2011)።

(a) *የጆሀፊው የትውልድ ስፍራ እንደምን ቀረበ?*

(b) *ንጉሱ ስለወሎ ያላቸው አመለንከት ምን ይመስላል?*

**2.**

ዘመን ዘመንን ሲሸረው
ትውልድም እንደምንጭ ጅረት
የእድሜ እንዝርቱን ሲያሾረው
ህይወትም በእስትንፋስ ጽላት፣ ኡደቷን ስታፋጥነው
ትናንትን እንደልቃቂት፣ እውስጧ ስታካትተው
ነገንም በተስፋ ስሜት፣ አሻግራ ስታስተውለው
መስከረም ለዳግም ልደት፣ የውበት ጃኖ ተላብሳ
ፍጡርን ስታነቃቃ፣ ከእንቅልፍ አለሙ ቀስቅሳ
ምድሪቱን ገነት አድርጋ፣ ከጉም ሽፏኗ ገላልጣ
በአደይ አበባ አስጊጣ
ሙሽራ መስላ ስትወጣ
እሰይ አበጀሽ እንበላት፣
ጉንጉናችንን እጥልቀን
በስሟ እንግጫ ነቅለን
የሷን ስጦታ መልሰን
ቄጠማችንን ጎዝጉዘን
እንቁለጣትሽ እያልን
መስከረም …….
የተሚጠጠ ሙት ተስፋ፣ ዳግም ባንቺ ላይ ሲያገግም
ኑሮም እስትንፋስ ስትዘራ፣ መጪ ዘመኗን ስታልም
ክዋክብትንም እንደ እንቁ፣ ፈነጣጥቋቸው ሰማዩ
ሜዳ ሸለቆሽ ከሩቁ፣ ስጋጃ ለብሰው ሲታዩ
ጊዜም ጉዞቷን ልታድስ፣ ሀሌታው ብላ ልትጀምር
አዲስ ፍኖቷ ሲበሰር
መስከረም ……..
የዘመን በኩር ማለዳ፣ የዶፍ በረዶ ማክተሚያ
የፀደይ ንጋት ማብሰሪያ
የደመና እንባ ማጠቢያ
መስከረም ……

መስፍን አሸብር፣ *ጠብ ፍቅር* ፣ (2008)::

(a) መስከረም በግጥሙ እንደምን ቀረበ?

(b) ገጣሚው የአንባቢው አመለካከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የተጠቀመባቸው ቴክኒኮች ላይ አስተያየት ስጥ?